# የ COVID-19 ክትባት ማጎልበቻ ክትባቶች ምንድን ናቸው?

## ጽሁፍ

*[የመሸጋገሪያ ሙዚቃ]*

*[ትረካ]*

አንድ ሰው ሙሉ በሙሉ ከተከተበ በኋላ ይህ ሰው በተለምዶ  ከፍተኛ ደረጃ የ COVID-19 መከላከያ ይኖረዋል።

ምንም እንኳን ክትባቶቹ ለከባድ ሕመም፣ ሆስፒታል ከመተኛት እና ለሞት የመጋለጥን እድል በመቀነስ ረገድ በጣም ውጤታማ ሆነው ቢቀጥሉም፣ አዲስ የወጣ መረጃ እንደሚያሳየዉ ፣ የክትባቶቹ የCOVID-19 ኢንፌክሽን  የመከላከያ አቅም በጊዜ ሂደት እንደሚቀንስ ያሳያል።

ከክትባቱ የተገኘው የመጀመሪያው መከላከያ መቀነስ ሲጀምር ፣  የመከላከያ አቅምን ለማሳደግ እንዲረዳ ማጎልበቻ ክትባት ተብሎ የሚጠራው ተጨማሪ ዶዝ ይሰጣል።

ይህ ተጨማሪ ዶዝ አንድን ሰው በበሽታ እንዳይያዝ ለመከላከል ተጨማሪ የሰውነት የበሽታ መከላከያ አቅም ያመነጫል።

ብዙ መደበኛ ክትባቶች ከፍተኛ ደረጃ መከላከያ ለማስገኘት ፣ ማጎልበቻ ክትባቶችን ይፈልጋሉ።

ለምሳሌ፡ ሰዎች በየ10 አመቱ  የቴታነስ ክትባት መከተብ አለባቸው።  ይህ ማጎልበቻ ክትባት ይባላል። የክትባቱ የመከላከያው አቅም በጊዜ ሂደት የሚቀንስ እንደመሆኑን ስለምናውቅ ፣ የበሽታ መከላከል አቅምዎን “ያጎለብታል”።

የ COVID-19 ክትባቶችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት health.mn.gov/covidvaccineን ይጎብትኙ።

*[የመሸጋገሪያ ሙዚቃ]*

Minnesota Department of Health
Communications Office
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-4989
health.communications@state.mn.us
www.health.state.mn.us

10/6/21 (Amharic)

*ይህን መረጃ በተለየ አቀራረብ ለማግኘት በሚከተለው ቁጥር ይደውሉ: 651-201-4989።*